በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

**ኅዳር 23፣ 2013 ዓ.ም.**
**አዲስ አበባ**

**ቀጣዩን ምርጫ በተመለከተ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር የተደረገ ውይይት**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በተገኘበት ቀጣዩን ምርጫ አስመልክቶ ከፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች እና ከሲቪክ ማኅበረሰብ ተወካዮች ጋር ውይይት አካሂደዋል። ውይይቱ ዐበይት ባለ ድርሻ አካላት ያላቸውን ሚና እና ኃላፊነት እንዲሁም የምርጫ ስርዓትን በሚያስቃኝ ገለጻም ቀርቧል። በጉጉት የሚጠበቀው እና ዐበይት ዴሞክራሲያዊ ተቋማት መሠረታዊ ለውጥ ማካሄዳቸውን ተከትሎ የሚከናወነው ታሪካዊ ምርጫ፣ ከ2010 አንስቶ ኢትዮጵያ በዴሞክራሲ ጎዳና የምታደርገው ጉዞ ዓይነተኛ ማሳያ ይሆናል።

የውይይቱ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ጨምሮ በርካታ ጉዳዮችን አንስተዋል፡-

- አስፈላጊዎቹ መሠረታዊ ጉዳዮች ባልተሟሉበት ሁኔታ ለምርጫ ያለ መጣደፍ
- ምቹ ሁኔታን መፍጠር
- ከምርጫው አስቀድሞ የሕግ የበላይነትን ማስከበር
- የምርጫ ታዛቢዎችን ጨምሮ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚያገለግል የምርጫ ደንብን ማዘጋጀት
- የሕጋዊ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ተሳታፊነት ማረጋገጥ
- የፖለቲካ ፓርቲዎች 'በጨዋታው ሕግ መሠረት' ተሳታፊ መሆናቸውን ማረጋገጥ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የውይይቱ ተሳታፊዎች ላነሷቸው ጥያቄዎች እና ሀሳቦች የሚከተሉትን ጨምሮ ምላሾችን ሰጥተዋል፡-

- ምርጫ ተኮር ውይይት በሚካሄድበት ጊዜ ሁሉም ፓርቲዎች በአቋማቸው እንዲጸኑና ምርጫን አስመልክቶ ምቹ ነባራዊ ሁኔታ የለም የሚል ምክንያት በመደርደር ከዚህ ቀደም እንደ ተስተዋለው ሀሳባቸውን እንዳይለዋውጡ፣
- ምርጫ ለዴሞክራሲያዊ ሂደት አንደኛው ዋነኛ መሠረት መሆኑን በማስታወስ፣ ሙሉ በሙሉ የተመቻቸ ነባራዊ ሁኔታ እስከሚገኝና የተፈለጉት ነገሮች እስከሚሟሉ መጠበቅ ምርጫ የሚካሄድበትን ጊዜ ይብሱን ወደ ፊት የሚገፋው መሆኑን፣
- እንከኖችን ለማስወገድ ጎን ለጎን ሥራዎችን እያቀላጠፉ ምርጫን ማካሄድ ዴሞክራሲያዊ መሆኑን፣
- የሕዝብን አመለካከተ በተመለከተ የሚነሱ ሀሳቦች ከእውነታው የራቁ እንዳይሆኑ፣ በመረጃ ላይ መመስረት አስፈላጊ መሆኑን፣
- ብዝሀነት ያላቸው እሳቤዎች የሚደመጡባቸውና ቀጣይነት ያላቸው የምክክር መድረኮች ለዴሞክራሲያዊ ሂደት በእጅጉ አስፈላጊ መሆናቸውን ለፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች አስታውሰዋል፣
- ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ በሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ሙስናን የመዋጋትን አስፈላጊነት አንስተዋል፣
- የቅድመ ምርጫ ችግር አፈታት ዘዴዎች ለውይይት እንደ ቀረቡ፣ ዕቅድ እንደ ወጣላቸውና ለሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ተግባራዊ እንደሚያደረግ ገልጸዋል፣

- በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሊቀመንበርነት፣ ከዐበይት ፖለቲካ ፓርቲዎች ተውጣጥቶ ፓርቲዎች የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመንግሥት በማቅረብ እንዲቀረፉ የሚሠራ ኮሚቴ መቋቋሙን አበረታተዋል፣
- ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሕግጋት በተጨማሪ፣ የብልጽግና ፓርቲ የምርጫ አግባብ ማዘጋጀቱን አስታውሰው ገዢው ፓርቲ ለዚህ ደንብ ተገዢ እንደሚሆን አስታውቀዋል። ብልጽግና ፓርቲ የራሱን ደንብ ያዘጋጀው ሁሉም አባላቱ ነጻ እና ፍትሐዊ ምርጫን እንዲያከናውኑ  በማስቻል፣ ለኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ምርጫ መሠረት እና ንድፍ በመሆን እንዲያገለግል ነው።
- ህወሓት መሠረተ ልማትን ያወደመ ቢሆንም፣ ሕዝቡም ለረዥም ጊዜ ቸል ተብሎ የኖረ ቢሆንም፣ የፌደራል መንግሥት ትግራይን መልሶ ለመገንባት ባለው ቁርጠኝነት እንደሚቀጥል፣ ለሕዝቡ አገልግሎት መሠጠቱ እንደሚቀጥል እና መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት እንደሚሠራ አስታውቀዋል፣
- የአማራ ክልል እና የትግራይ ክልል እንደ ተጋጩ ተደርጎ የሚነገረው ትርክት፣ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ያለውን ጥብቅ ግንኙነት የሚያጣጥል ስለሆነ፣ እውነታው እንዲስተዋል አሳስበዋል፣
- ለረዥም ጊዜ የዘለቀ የመሬት ባለቤትነት ውዝግብ መኖሩን አስመልክተውም፣ የሁለቱን ክልል ህዝቦች ሀሳብ በምክክር አስደግፎ፣ እንዲህ ያሉትን ጉዳዮች የማጥናት ኃላፊነት ያለበት የአስተዳደር ወሰን እና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን በሚያቀርበው ጥናት መሠረት ሕግና አግባብን በተከተለ መንገድ ብቻ የሚፈቱ መሆኑን ገልጸዋል፣
- በአመጽ ለውጥ ለማምጣት መሞከር እንደማይሠራ ተገንዝበው፣ ሁሉም አብሮ በመሥራት የሰላም ጠባቂዎች እንዲሆኑ አሳስበዋል፣
- የፌደራል መንግሥት ቀጣዩ ምርጫ ነጻ እና ፍትሐዊ እንዲሆን አስፈላጊውን ሁሉ የሚያደርግ መሆኑን በአጽንኦት ተናግረዋል።

//